አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ ት/ፅ/ቤት የ6ኛ ክፍል የሁለተኛ መንፈቅ ዓመት ግብረገብ ሞዴል ፈተና

ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት :- 40

የተፈቀደ ሰዓት :- 1 ሰዓት

የፈተና ትዕዛዝ

- ትዕዛዙን በአግባቡ ካነበባችሁ በኋላ ጥያቄ ካላችሁ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ለፈታኝ መምህር መጠ የቅ።
- ይህ ፈተና 40 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ለዚህም ፈተና 1ሰዓት ተፈቅዳል ።
- ትክክለኛውን መልስ ከመረጣችሁ በኋላ በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አስቀምጡ።
- እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት አማራጮች ተሰጥቷል። ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በመልስ መስጫ ቦታ ፃፉ።
- ለመኮረጅ ሆነ ለማስኮረጅ መሞከር ፈተናው ሙሉ በሙሉ ያሰርዛል።

" ፍቃድ ስታገኙ ወደ ሚቀጥለው ገፅ ግለጡ "

2016 ዓ.ም

1. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አንዱ ከግብረገብ ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ አይመደብም ።

ሀ. የሰውን ልጅ ያበለፅጋል። ሐ. ግጭቶችን ለመፍታት ይረዳል።

ለ. ህብረተሰብን ከመለያየት ይታደጋል። መ. የሰዎችን ስቃይ ይጨምራል።

2. የህግ ተገዥነት ለዜጎች የሚሰጠው ጠቀሜታን የማይገልፀው የቱ ነው?

ሀ. በዜጎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለህይወታቸው ጥበቃ ይሰጣል።

ለ. ዜጎች በሙሉ በነፃነት ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ ይረዳል።

ሐ. ሀብት ያላቸውን ብቻ መብታቸው እንዲጠበቅ ይረዳል።

መ. በዜጎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ያደርጋል።

3. ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ባህሪ ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. የሌሎችን ክብር አለማግኘት። ሐ. በቤተሰብ ዙሪያ አሉታዊ ምስል መፍጠር።

ለ. ራስ ወዳድ መሆን። መ. በማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት።

4. ከሚከተሉት ዉሰጥ አንዱ ስልጣን ባላቸው ሰዎች የሚፈፀም ያለመታመን ድርጊት ነው?

ሀ. የግብር ስወራ ለ. ጉቦ መቀበል ሐ. የዝምድና ወገተኝነት መ. ሙስና

5. የግብረገብ ምዕሉነት መጓደል የሚታይባቸው ሰዎች ከሚከተሉት ባህሪያት ውስጥ አንዱን ያሳያሉ?

ሀ. አስመሳይ መሆን ለ. ቃልን ማክበር ሐ. በራስ መተማመን መ. ሚስጥር መጠበቅ

6. ከሚከተሉት አማራጮች አንዱ ከህግ መስፈርቶች ውስጥ አይመደብም?

ሀ. ወጥነት ለ. ቋሚነት ሐ. ተለዋዋጭነት መ. የፍትህ እጦት

7. ከሚከተሉት ውሰጥ አንዱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫ አይወክልም?

ሀ. በሀገር መኩራት። ሐ. ሀገርን ለጠላት አሳልፎ መስጠት።

ለ. የባለቤትነት ስሜት መያዝ ። መ. ሙስናን መዋጋት።

8. ቁጠባ ለተማሪዎች ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ውሰጥ የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ለተማሪዎች የሙያ ትምህርት የግዛል። ሐ. ለትምህርት ቤት ክፍያ ይውላል።

ለ. ለድንገተኛ ወጪ ይጠቅማል። መ. አልባሌ ለሆኑ ነገሮች ማዋል።

9.ከሚከተሉት ውስጥ የማህበረሰብ የጋራ ጥቅም ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ሀ. የህዝብ መሰረተ ልማት ሐ. የህዝብ ትምህርት ቤቶችና ቤተ_መጽሐፍት

ለ. የህዝብ ትራንስፖርት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

10. ከሚከተሉት ውስጥ አንድ ሰው ሰለነገሮች ባለው መሠረታዊ ግላዊ እምነት ከእለት ወደ እለት በሚፈፅማቸው ድርጊቶች መካከል ኢ-ተለዋዋጭ አቋምን የማሳየት ብቃት _____ይባላል ፡፡

ሀ. ስርዓት ዓልበኝነት ለ. ጉቦ መስጠት ሐ. ምሉዕነት መ. የዝምድና ወገንተኝነት

11. በዜጎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለህይወታቸው ለመብታቸውና ለንብረታቸው እኩል ዋስትና እንዲኖራቸው ማድረግ_____ይባላል፡፡

ሀ. የህግ ከለላ ለ. የህግ የበላይነት ሐ. ለህግ ተገዥነት መ. ህገ መንግስት

12. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምዕሉነት መላበስ የሚያመጣው ጥቅም የቱ ነው?

ሀ. አስመሳይ መሆንን ሐ. ጓደኛ አልባ መሆን

ለ. ማህበራዊ ትስስርን ማድከም መ. የሌሎችን ክብር ማግኘት

13. ከሚከተሉት ውስጥ የማህበራዊ በጎ አገልግሎት ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን አቅመ ደካሞች መርዳት

ለ. መጠለያቸውን መጠገን እና የተራቡትን ምግብ ማብላት

ሐ. ነፃ የህግ አገልግሎት መስጠት

መ. ህዝብን ከህዝብ ማጣላት

14. ሰዎች ሀገራቸውን መውደዳቸው ከሚያሳዩበት መንገድ ውስጥ አንዱ አይካተትም ፡፡

ሀ. በሰንደቅ ዓላማ ለ. በብሔራዊ መዝሙር ሐ. ሀገርን ማዋረድ መ. በአርበኝነት

15. ከሚከተሉት ውስጥ ሰዎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚያገኙት መብት ነው?

ሀ.የመምረጥ እና የመመረጥ መብት ሐ. የመደራጀት መብት

ለ. ሰብዓዊ መብት መ. ዲሞክራሲያዊ መብት

16 ለኢትዮጵያ ብሎም ለአፍሪካ የመጀመሪያውን የኦሎምፒክ ወርቅ ያስገኘው ማነዉ ?

ሀ. ኃይሌገ/ስላሴ ለ. ስለሺ ስህን ሐ. ሻንበል አበበ ቢቂላ መ. ቀነኒሳ በቀለ

17. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የመልካም ባህሪ ምንነትን የማያሳይ ምሳሌ የቱ ነው?

ሀ. ከብር መስጠት ሐ. ሀላፊነትን መወጣት

ለ. ሀላፊነትን መሸሽ መ. ተጠያቂነት

18. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ሰላም ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰላምን የማስጠበቅ ሂደት መቋጫ የለውም።

ለ. ሰላም ሊረጋገጥ የሚችለው በመንግስት ባለስልጣናት ብቻ ነው።

ሐ. ሁሉም የሰው ልጆች ሰላም ለህይወታቸው ያስፈልጋቸዋል።

መ. ለአንድ ሀገር ሰላም ወሳኝ ነው።

19. ውጤቱ ምንም ሆነ ምን እውነትን የመናገር ብቃት _____ይባላል

ሀ. ድፍረት ለ. ታማኝነት ሐ. ሃቀኝነት መ .እውነተኛነት

20. ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ስነ-ምግባር መገለጫ የሆነው የትኛው ነዉ?

ሀ. ህገ-ወጥ ተግባራትን አለመቃወም ሐ. ህገወጥ ድርጊት ውስጥ አለመግባት

ለ. የሌሎችን ሰዎች መብት መንካት መ. ፈተና ከሌሎች መኮረጅ

21. አንድ ሰው ትክክል ነው ብሎ የሚያምንበትን ነገር እንዲተገብር የሚያደርግ ውስጣዊ ችሎታ ነው።

ሀ. ሃቀኝነት ለ. ድፍረት ሐ. ታማኝነት መ. እውነተኛነት

22. የሚከተሉትን ጉዳዮች መሰረት አድርጎ መንግስት ግብር ይሰበስባል ።

ሀ. ከፋይናስ ገቢ ሐ. ከቋሚና ዋጋ ካላቸው ተንቀሳቃሽ ንብረቶች

ለ. ከግለሰቦች የንግድ ትርፍ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

23. ቁጠባ ለተማሪዎች ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው።?

ሀ. ለተማሪዎች የሙያ ትምህርት ያግዛል ሐ. ለትምህርት ቤት ክፍያ ይውላል

ለ. ለድንገተኛ ወጪ ይጠቅማል መ. አልባሌ ለሆኑ ነገሮች ማዋል

24. ለሰላምና መተባበር ማደግ ትልቁን ሚና የሚጫወቱት ከማህበረሰብ ቀጥሎ

ሀ. ፓሊስ ለ. ዳኞች ሐ. ወታደር መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

25. ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዢ የሆነ ዜጋ ባህሪያት ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ለህግ ተገዢ የሆነ ዜጋ ህግ ሲጣስ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል።

ለ. ለህግ ተገዢ የሆነ ዜጋ የሀገሪቱን ሰላም ይጠብቃል።

ሐ. ለህግ ተገዢ የሆነ ዜጋ የሀገሪቱን ህግ የማወቅ ግዴታ የለበትም።

መ. ለህግ ተገዢ የሆነ ዜጋ መብቱንና ግዴታውን ያውቃል።

26. የመልካም ስነ-ምግባር ባህሪ መገለጫዎች ሊሆን የማይችለው የቱ ነው?

ሀ. ስራን መውደድ ሐ. ሀገርንና ህዝብን መውደድ

ለ. የመልካም ስብዕና ባለቤት መሆን መ. መልሱ የለም

27. ከሚከተሉት ዉስጥ ሰላማዊ ባህሪ ምሳሌ የማይሆነው የቱ ነው?

ሀ. አብሮነት ለ. ትዕግስት ሐ. ውይይት መ. አለመከባበር

28. አንድ ሰው ለሀገሩ ጀግና ነው ስንል?

ሀ. ህይወቱን ለሀገሩ ለመስጠት ፍቃደኛ ነው። ሐ. ለማህበረሰቡ ክብር የለውም።

ለ. የሀገሩን ሀብት ይበዘብዛል። መ. በሀገሩ ያፍራል።

29. ከሚከተሉት ውሰጥ የመተባበር ጠቃሚ እሴት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. አንድነት ለ. ግልፅነት ሐ. ሌሎችን መርዳት መ. ሌሎችን አለማክበር

30. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራል። ሐ. ቃላችንን እንድናከብር ያግዛል።

ለ. ችግር የመፍታት ክህሎትን ያዳብራል። መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

31. ለህግ ተገዢ መሆን ለምን ያስፈልጋል ?

ሀ. ህግ ሰዎችን ከጉዳት ስለሚከላከል ሐ. ህግን አለማወቅ ከተጠያቂነት ስለማያድን

ለ. ህግ ደህንነታችንን ስለሚያስጠብቅ መ. ህግን ለመጣስ

32. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሀገርን መውደድ ምንነት አይገልፅም ።

ሀ. በሀገር ባህል መኩራት። ሐ. በህዝብና በታሪክ መኩራት።

ለ .በቀኝ ግዛት ባለመገዛታቸው መሸማቀቅ። መ. የሰው ዘር መገኛ በመሆናቸው ይኮራሉ።

33. ከሚከተሉት መካከል መልካም ባህሪን ለማሳደግ የሚያስችለዉ የቱ ነው?

ሀ. የት/ቤት ህግና ደንቦችን ማክበር፡፡ ሐ. ሀላፊነትን መውሰድ፡፡

ለ. ራስን መቆጣጠር፡፡ መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

34. የራስን ሰዓትንና ጉልበትን በሙሉ ፈቃደኝነትና ቁርጠኝነት ማዋል_____ማለት ነው፡፡

ሀ. መቻቻል ለ. መከባበር ሐ. በጎ አድራጎት መ. ማህበራዊ ጥቅም

35. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ምንነትን አይገልፅም ፡፡

ሀ. የማህበራዊ ችግሮችን አይፈታም፡፡

ለ. በማህበራዊ እንቅስቃሴ ማህበረሰቡን ወደ አንድ ያመጣል፡፡

ሐ. ለችግሮች መፍትሄ ያመጣል፡፡

መ. ማህበራዊ እንቅስቃሴ በቡድን ወይም በማህበር ይተገበራል፡፡

36. ሰላም ለሰው ልጆች ከሚሰጠው ጥቅም ውስጥ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ከሁከት ነፃ መሆን ፡፡ ሐ. መሰረተ ልማትን ማውደም፡፡

ለ. ሌሎችን መጨቆን ፡፡ መ. ሰዎችን መገረፍ፡፡

37. ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ባህሪ ምሳሌዎች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ትሁት መሆን፡፡ ሐ. ስህተትን አለመቀበል ፡፡

ለ. ጥሩ ጓደኛ መምረጥ ፡፡ መ. ፍቃድ መጠየቅ ፡፡

38. ሰውን የሚያከብሩ ሰዎች ባህሪ የሆነዉ የቱ ነው?

ሀ. ትዕቢተኛ ናቸው፡፡ ለ. ሩህሩህ ናቸው፡፡ ሐ. አስመሳይ ናችዉ፡፡ መ. ኩራተኛ ናቸዉ፡፡

39. መልካም ባህሪ አለመላበስ የሚያስከትላቸው መጥፎ ውጤቶች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. ፈተና አለመኮረጅ ፡፡ ሐ. ታማኝ አለመሆን ፡፡

ለ. መዋሸት ፡፡ መ. የት/ቤት ንብረት ማውደም ፡፡

40. ለአንድ ሀገር ማህበረሰብ ወጥቶ መግባት ፣ መስራት እና መረጋጋት የሚሰጠው _____ይባላል፡፡

ሀ. ተስፋ ለ. መተባበር ሐ. ሰላም መ. ፅናት